# በዋለልኝ ስም ሀገርንና ትውልድን ጠቅልሎ ለወያኔ ሃጢአት ማበሻ ማድረግ

ከአህመድ ይማም

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ወያኔ ያደርግ የነበረው በተቃዋሚ ስም ቅጥረኛው የሆኑ ግለሰቦችን በመካከላችን አሰማርቶ ሕዝባዊ ትግሉን ማዘናጋት፣ እርስ በእርስ ማባላት ነበር። በተቃዋሚ ስም ገንዘባችን እና ጊዜያችንን በመውሰድ ነበር የሚያስገመግምበትን ሕዝባዊ ትግል ምጣት ለማዘግየት የሚጥረው። አሁን አሁን ደግሞ ዱሮም ስማቸው እንጂ ምግባራቸው አፍቃሪ ወያኔያዊነት ("ደቀ-አሉላነት") ባልተለያቸው አንዳንድ ድረ-ገፆች አማካይነት ታሪክና ገድል ለመቀማት ሲጥር ይስተዋላል። ገንዘባችንና ጊዜያችንን ለመስረቅ ያደርግ ከነበረው አልፎ ልባችንንም ሊሰልብ እየጣረ ነው። በተለይ ይህንን መጣጥፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ "ዋለልኝ መኮንንና የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ኢትዮሚዲያ ላይ የወጣው ጽሑፍ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው።

ይህ ጽሑፍ ገና ሲጀምር፡

"በቅርቡ በየዓመቱ የሚከበረው ብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓልና አምስተኛው ኣለም አቀፍ የፌዴሬሽን ጉባዔ በአገራችን ሲስተናገድ ሰንብቷል። የብሄር ብሔረሰቦች ቀን እንደ በዓል መከበሩ አስፈላጊነቱ በኤቲኒክ መርህ ላይ የተመሰረተውን የፌዴራል ሥርዓት አጽንዖት ለመስጠት የታሰበ መሆኑ ቢታወቅም ግና ዋናውና አሌ የማይባል አዲስ ተዋጽዖው ማንነታቸው ተረስቶና ተንቆ በገዛ አገራቸው የሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የነበራቸው ሕዝቦች አዎን አለን፣ ነበርን፣ እንኖራለንም ብለው ራሳቸውን በአደባባይ የሚገልጹበት፣ ባህላዊ እሴቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበት በጋራ የፌስቲቫል ስሜት አንድነታቸውን ተስፋቸውንና የአገራቸውን ሰላም የሚዘክሩበት ቀን መሆኑ ነው (መስመር የእኔ)።" ይልና፡ አስከትሎ፡

"በመሆኑም ነው በአሁኑ ጊዜ መላው የኢትዮጵአ ህዝብ ትኩረቱንና ጥረቱን ለእድገትና ለልማት በማድረግ በአንድ ልብ ተነስቶ ማየት ልብ የሚያሞቅ ተስፋ የሚፈነጥቅ ስሜት በሁሉም ዘንድ የሚፈጥረው። በአንድ ጥይት ሁለት ገድል ለመጣል ሁሉም የዴሞክራሲ ናፋቂና አገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ ይህን ርብርቦሽ ማገዝና መርዳት ሊመካበት የሚገባው ተግባር ነው።"

በማለት ይደመድማል። በወያኔ ስም ባርኮ በመጀመር፣ የሕዝብን ታሪክ ገድሎ ሲያትት ከቆ በሁዋላ፣ በሕዝብ ስም ምሎ እየተገዘተ - እስከዛሬ ለሀገር አንድነትና ለሕዝብ መብት የተደረጉ ትግሎችንና መስዋዕትነት የከፈሉ የሕዝብ ልጆችን እረግሞ፣ የወያኔ አገዛዝ ይቀጥል ዘንድ መርቆ ይደመድማል።

ለመሆኑ ገና ከመነሻው የወያኔው አገዛዝ ትርፍ አድርጎ የሚያወድሰው የሕዝብ የዜግነት እኩልነት፣ አንድነትና ተስፋ ኢትዮጵያ ምድር ነው ወይስ ሌላ ክፍለ-ዓለም ነው ላይ ያለው? በዘር በሃይማኖታቸው ሰበብ በአርባ ጉጉ፣ በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በወተር፣ በጎንደር፣ በጋምቤላ፣በኦጋዴን ወዘተ በጠቅላላው በመላው ኢትዮጵያ መቶዎችን የቀጠፈው፣ ያፈናቀለው፣ አሁንም በየክልሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንን እንደ ሁለተኛ ዜጋ የሚያስኖረው ወያኔ ወለዱ የፌዴራል ሥርዓት ተብዬው አይደለምን?

እርግጥ ነው፣ ፀሐፊው መለስ ሲቀነስ (መለስ ማይነስ) በሆነ ጥገናዊ ለውጥ ያለውን ሥርዓት ለማስቀጠል ከተቋቋመው ከዓረና ትግራይ ሰዎች አንዱ ስለሚመስሉ፣ ኢትዮሚዲያም ይህንኑ ለማገዝ የተቋቋመ ድረ-ገጽ ስለሆነ፤ የእነሱ በሥልጣን መፏለል፣ የሌላውን በወያኔ አድሏዊ አገዛዝ መጨቆን፣ የእነሱ በምቾትና በቁንጣን መላ ቅጥ ማጣት፣ የሌላውን ማጣት መገርጣት፣ መራብ መጎሳቆል፣ የእነሱ ጮቤ መርገጥ፣ የሌላውን ማዘንና መከፋት ላያሳያቸው ይችላል። በእኛ በኩል ግን የናንተ የፌዴራል ሥርዓት በትግራይ ህዝብ ስም የሚነግዱ ጥቂት ሰዎችን የበላይነት ያነገሰ፣ በ 1928

ዓ. ም. ጣሊያን ወረራ ባካሄደ ጊዜ ለከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲው ይረዳው ዘንድ በቋንቋ ላይ ብቻ ተመስርቶ ያዘጋጀውን የአስተዳደር ካርታ ከተቀበረበት አውጥቶ ሥራ ላይ በማዋል፣ በሀገራችንና በሕዝባችን አንድነት ላይ የተሰበቀ ጦር ነው። በረጅም ጊዜ ሂደት ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን በመግደል፣ ታላቋ ትግራይ ትግርኝ ሪፑብሊክን ለመመስረት እያደረጉ ያለውን ዓይን ያወጣ ፖሊሲና አገዛዝ እንዳናይ የሚረጩልንን ልቦና ሰላቢ መርዝ ከመጋት እምቢዮው ማለት አለብን። ትላንት ከትላንት ወዲያ የጠባብ ብሔርተኞችን ለምሳሌ የዚያድ ባሬ ጄኔራል የሚመራውን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ድርጅትን፣ ኦነግን ወዘተ አርበኞች ብለው ከበሮ ከመደለቅ አልፈው ዛሬ ደግሞ ወያኔንና አንቀጽ 39ኙን የእግዚአብሔርና የትውልድ ስጦታ ስለሆኑ እናክብራቸው በሚሉን የበግ ቆዳ ለባሽ ዲኩላዎች የሆኑ የፕሮፓጋንዳ ድረ-ገፆቻቸው፣ የኢትዮሚዲያ ዓይነቶቹ ከፀረ-ወያኔው ጎራ ናቸው ብለን መጃጃሉን ልናቆም ይገባል። ደም ከውሃ ይወፍራል በሚል የጠበበ ዕይታቸው ቁርጡ ቀን ሲመጣ ሰልፋቸው ከነማን እንደሚሆን በግልጽ እያመላከቱን ስለሆነ ልብ ያለው ልብ ይበል።

ቀደም ሲል ያነሳሁት ኢትዮሚዲያ ላይ የወጣው ጽሁፍ በጠቅላላው በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ በተለይም የአፄውን፣ የደርግንም ሆነ አሁን ያለውን አገዛዝ/ሥርዓት ከመሠረቱ ለመቀየር የተካሄደውንና እየተካሄደ ያለውን ትግል ጠቅልሎ ዋለልኝ መኮንን የሚል ስም በሰጠው ሣጥን ውስጥ ሊያስቀምጠው ይጥራል። ግና ጽሑፉ የታሪክ ሐቅ የጎደለው፣ ከተጠይቅ አንፃር የተምታታበት (እርስ በእርስ በሚቃረኑ ሀሳቦች የታጨቀ)፣ በአቋምም ለወያኔ ያደረ ነው።

ለማስታወስ፣ ዋለልኝ መኮንን ህዳር 8 ቀን 1962 ዓ. ም. "On the Question of Nationalities in Ethiopia" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጽሑፍ፡

**“The main purpose of this article is to provoke discussions on the "sacred", yet very important issue of this country-the Question of Nationalities. The article as it was prepared for a special occasion (where detailed analysis was due to time and other inconveniences impossible) suffers from generalizations and inadequate analysis. But I still feel it is not mediocre for a beginning. I expect my readers to avoid the temptation of snatching phrases out of their context and capitalizing on them. Instead every point raised here should be examined in the light of the whole analysis.”**

በማለት ጀምሮ የሚያትተው በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ ነው። ጉዳዩን እንወያይበት ነው ያለው። ስለጽሁፉ አወጣጥና ስለታሪካዊ ሁነቱ ዛሬም ሀቁን የሚያውቁ የትውልዱ አባላት ስላሉ ተገቢውን መልስ እንደሚሰጡ ተስፋ  አለኝ። ከዚህ በፊትም የሰጡበት ስላሉ፣ ዳግም ጽሁፎቻቸውን ማንበቡ ለግንዛቤ ይጠቅማል።  ግና ዛሬም ድረስ እያመሰን ያለውን የተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ክፍሎች (ብሔረሰቦች) ዕኩልነት ጉዳይ አንስቶ መወያየት ሀጢአቱ ምንድነው?  ያን ጊዜ ጉዳዩን ያነሱት ዋለልኝም ሆኑ ጓደኞቹ የነበረው የእኩልነት እጦት ችግር መፍትሄ ካላገኘ የሚያስከትለውን ጦስ፣  ዘመንና ትውልድ ተሻግረው፣ ቀደም ብለው በማየታቸው፣ ባለራዕይ ሊባሉ፣ የጨለማ ዘመን ኩራዞች ሊባሉ ነው የሚገባቸው።  አሁን ላለንበት ችግር ተጠያቂ በማድረግ፣ ያለፉትንም ሆነ ሀገሪቷንና ህዝቧን ወደተሻለ አስተዳደር እንዳይራመዱ ቀፍድዶ የያዘውን ዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ ከደሙ ንጹህ  ለማደረግ መሞከር ሀቅን መካድ ነው።

ዋለልኝ በጽሑፉ መግቢያ ላይ "አንባቢያኔ ለውይይት ያቀረብኩትን ይህን ጽሑፍ ሐረጋት በመልቀም፣ ከአገባባቸው ውጭ ትርጓሜ በመስጠት ፀጉር በመሰንጠቅ ፈንታ ያለብንን ሀገር አቀፍ ችግር በምሉዕነት ከመመርመር አንፃር ሊወያዩበት እንደሚሹ ተስፋ አደርጋለሁ"  በማለት ከዛሬ 41 ዓመት

በፊት ያሰቀመጠውን እኒሁ የኢትዮሚዲያ ፀሐፊ ልብ ሊሉት አልፈቀዱም። አዋዝተው በማር የተለወሰ ውሸት ሊመግቡን ሲንደረደሩ "የዛሬው ኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ጥንስሱ የተቋጠረውና የንድፈ-ሃሳብ ቀመሩ የተቋጨው ገና በሰባዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ሲሆን ፋና ወጊ በመሆን ቁልፍ ሚና የተጫወተውም ዋለልኝ መኮንን ነው። ዋለልኝ መኮንን የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም የነፍስ አባት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በኢትዮጵያ ማርክሲዝምን በማስፋፋቱም ሆነ በመተግበሩ የተካኑ እንደ ሃይሌ ፊዳና የመሳሰሉ የማርክሲዝም ሊቃነ-ጳጳሳት ቢኖሩም ዋለልኝ መኮንን ግን የማርክሲዝምን ጠበል ከኢትዮጵያ አፈር ጋር አሃዱ ብሎ ያዋሀደ የመጭውንም ዘመን ብስራትና መርዶ የነቀሰ ኢትዮጵያዊው የማርክሲዝም መጥምቁ ዮሐንስ ነበር።" በሚለው አይነት ከድንጋይም ድፍን የሆነ አባባላቸው ወያኔን ከደሙ ንጹህ ለማድረግ እና ሃጢአቱን በዚያ ትውልድ እና በማርክሲዝም ርዕዮተ-ዓለም ላይ ለመለጠፍ ሞክረዋል። አሁን ሀገራችን ላይ እየተገበረ ያለው ፌዴራላዊ አገዛዝ ካርታ የተቀዳው የጣሊያን ወራሪ ሃይል በ1928 ዓ. ም. ካዘጋጀው የከፋፍሎ መግዣ፣ በቋንቋ ሸንሻኝ ካርታ ነው። ቀጂዎቹም፣ ሥራ ላይ አዋዮቹም ደግሞ ህዝብ በግልጽ እንደሚያውቀው ትላንትም ዛሬም የደደቢት ዘረኛ ዛር የሰፈረባቸው ወያኔዎች ናቸው። ስማቸውም መለስ፣ ስባሃት፣ ስዬ፣ ገብሩ፣ አለምሰገድ፣ አረጋሽ ወዘተ ይባላል። ሁሉንም እንደየሥራው በመስጠት ፈንታ ዋለልኝንና የዚያን ትውልድ ባለራዕይ ጀግና አባላት ዳግም አስነስቶ ወያኔያዊ መንፈስ አልብሶ ለአሁኑ ችግራችን ተጠያቂ ለማድረግ መሞከር ትርፉ ትዝብት ነው። ህሊና ላለው።

ፀሐፊው ክሳቸውን የሚደረድሩበት ያ መከረኛ ታጋይ ትውልድ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረ፣ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለኢትዮጵያ መስዋዕት የሆነ የመሆኑን ሐቅ ሊክዱት አይችሉም። ልክ ከእምሃ-አልቦ መጥቶ፣ በእምሃ-አልቦ አስቦ፣ በእምሃ-አልቦ የነበረ አድርገው ሊያስቀምጡት መሞከራቸው በምኒልክ ጊዜ የደነቆረች ምልኒልክ ይሙት እንዳለች ትሞታለች እንደሚባለው በደርግ ጊዜ

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ አሁን ደግሞ በድምፂ ወያኔ የሚቀርበውን ክስ ነው ሊግቱን የሞከሩት።

ሀቁ ግን ያ ትውልድ በቤተሰቦቹ፣ በጎረቤቶቹ፣ በአካባቢው፣ በትምህርት ቤቱ በጠቅላላው በአደገበት፣ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ለነበሩት የሀገሩ ችግሮች መፍትሄ ነው ብሎ ባመነበት መስመር ነው የታገለው። ከሳሾቹ ለዚሁ ክርክራቸው የሚያቀርቡት ማጠየቂያ ትውልዱ በኢትዮጵያዊነት ባልተገራ የባዕድ ሥርዓተ-ትምህርት ያለፈ በመሆኑ ሰበብ የተከሰተ በሽታ እንደሆነም ሊያሳምኑን ሲጥሩ ይስተዋላል። እንደዚህ ዓይነት እጅግ አጠቃላይ ክስ ከታሪክም ሆነ ከማህበረሰብ ሳይንስ ትንታኔ አኳያ ሚዛን የማያደፋ ነው። በየሀገራቱ የሚሰጡ የተፈጥሮም ሆነ የማህበረሰብ ሳይንስ፣ የቴክኖሎጂም ትምህርቶች ዓለማቀፋዊ ብሄራዊውም ፀባዮች ይኖራቸዋል። የወቅቱ ሥርዓተ ትምህርት ከየትም ይምጣ ከየት፣ የምንሔ ሀገርም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ በሰው ልጅነታቸው የሚጋሯቸው ብዙ ነገሮች ስላሉ አዲሱ ትምህርት ለሀገራችን ምንም የሚረባ ቁምነገር አያስጨብጥም ነበር ማለት ውሃ የሚቋጥር አይመስለኝም። ዋለልኝም፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ ኢሕአፓ፣ ግንቦት 7፣ ኦነግም፣ ሌላው ቀርቶ ወያኔም የሀገራችን አገዛዝ ብልሹነት የቀፈቀፋቸው ናቸው። ደግሞም ግን እጅግ በጣም የተለያየ ግብ ሰንቀው የተነሱ ናቸው። በታሪክ ትርጓሜም ሆነ በመፍትሄ አሰጣጥ ላይ ምንም የማይገናኙ የዘመናዊ አትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን በተለይም ከነመንግሥቱ ንዋይ የ1953 መፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ጀምሮ የተካሄዱትን ዋለልኝ መኮንን በሚል አንድ ሙቀጫ አስገብቶ ለመውቀጥ መሞከር እሪ በል ተንታኝ ያሰኛል። አማርኛ በሚነገርበት አካባቢ ተወልዶ፣ በኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ያደገው ዋለልኝም ሆኑ ጓደኞቹ የብሔረሰቦችን ብሶት እንወያይበት ብለው ወደ አደባባይ ሲያወጡት፣ በባሌ፣ በትግራይ፣ በጎጃም፣ በኤርትራ ወዘተ ቦግ ብልጭ የሚል ጭቆና የወለደው አመጽ ይታይ ነበር። ለሚያስተውል ህሊናም ሀገሪቱ የተጋፈጠባትን አደጋ አመላካች ነበር። በአጠቃላይ አፄውንም ሆነ ደርጉን፣ አሁንም ወያኔን

በመቃወም የተካሄደው  እና እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ ትግል መሪ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ናቸው።

ዛሬ ምዕራባዊያኑ የመለስ ጌቶች የሚያደርጉትን ጣልቃ-ገብነት እንደምንቃወመው ትላንትም ያ ትውልድ በአፄው ወቅት የነበረውን የአሜሪካንን በውስጥ ጉዳያችን ገብቶ መፈትፈት ተቃውሟል።

ትላንትም ዛሬም ትግሉን የሚየካሂደው ከህዝቡ ከሰራተኛው፣ ከገበሬው፣ ከሴቱ፣ ከወንዱ ጋር ሆኖ እንጂ   በእድሜ ክልል ተገድቦ እንዳልነበረ እና አሁንም እንዳልሆነ ልብ ሊሉት ይገባል።  ትላንትም ዛሬም ትግሉ ወጣቱንም ጨምሮ የመላው ሕዝብ ነበር፣ ነውም።

ትላንትም ዛሬም የተነሱትና መልስ ያላገኑት የሕዝብ ጥያቄዎች ሕዝባዊ መንግሥት፣ መሬት ለአራሹ፣  ሕዝብ  የሥልጣኑ ባለቤት ይሁን፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ ወዘተ መብቶች ይፈቀዱ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፣ እኩልነትና ፍትህ ይረጋገጡ ወዘተ የሚሉት ናቸው።

የዋለልኝም ሆነ የዚያ ትውልድ ከሳሾች ብዙ  ጊዜ የሚሰነዝሩት ክስ ግራዎች ናቸው፣ የማርክሲዝም ርእዮት አራማጆች ናቸው የሚል ነው።  እኒሁ የኢትዮሚዲያ ፀሐፊም በዚሁ የተለመደ ዘይቤ፡

“ዋለልኝ መኮንን እንደ ግርማሜ ና መንግሥቱ  ንዋይ በ Medieval ዓለም ውስጥ የነበረው ጨቋኝ ፊውዳል ሥርዓት ላይ ያመፀ ህይወቱንም ነፍሱንም ለትግሉ አሳልፎ የሰጠ ብርቅና ድንቅ ከሚባሉት የተማሪዎች ንቅናቄ ኮከብ መሪዎችና ተዋንያን መካከል አንዱ ነው።  ዋለልኝ የትውልዱ ቋሚ መለዮ የሆኑት ባህርያት ማለትም ስርነቀልነት፣ (iconoclastic)፣ ማርክሲስትነትና መስዋዕትነት ሙሉ መገለጫ ተምሳሌ ነው" ብለው እንደማሞገስ ያደርጉና

በሚቀጥሉት አንቀፆች ደግሞ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት ችግር ሁሉ ተጠያቂ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሱን በሰፊው ያትታሉ።

"የዋለልኝ መንፈስ ባለፉት አርባ ዓመታት የኢትዮጵያን የፖሊቲካ መድረክ የተቆጣጠረና ለሚቀጥሉትም አስርተ ዓመታት ጥላውን እንዳጣለ የሚቆይ መንፈስ ነው። ... ዋለልኚዝም የኢሕአፓን የመሳሰሉት፣ የኦነግና የመሳሰሉት ዳዊት ነው። ዋለልኚዝም የኢህአደግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መሰረት ነው። ...ያለ ዋለልኝ መኮንን ኢህአፓን ወይም ኢሰፓን ማሰብ አይቻልም። ከኢህአደግ እስከ ኦነግ፣ ከመድረክ እስከ ግንቦት ሰባት ያሉትን ድርጅቶች ማሰብና ማወቅ አይቻልም። ... በኢትዮጵያ ከላፉት ሰላሳና አርባ አመታት አንስቶ ሁሉም ዜጎች የሚመኩበትና የሚኮሩበት፣ ቢያንስ ሁሉም ተዋንያን በእኩል የሚሳተፉበት፣ ቢያንስ ከሞላ ጎደል የሆነ ስርዓት ለመፍጠር መንገዱ የረዘመበት ዋንኛው ምክንያት በዋለልኝ ባህል ምክንያት ነው። ኢህአደግ በምንም ተአምር ከአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ በስተቀር ሌላ ምርጫ እንዳይኖረው ያደረገውና የሚያደርገው የተፈጠረበት አስኳል DNA ዋለልኝዝም በመሆኑ ነው። የተቃዋሚ ድርጅቶች ርስ በርስ የሚቆራቆዙበት ምክንያትና አልፎም ማናቸውም ቢሆኑ ለስልጣን ቢበቁ ከኢህደግ ርቀው የተሻሉ የማይሆኑበት ምክንያት የተጸነሱበት ማህፀን የዋለልኝዝም ባህል ውስጥ ስለሆነ ነው። ኦነግን ሰላሳ ዓመት ዱር ለዱር የሚያዞረው፣ ግንቦት ሰባትን ለፋኖ ተሰማራ ያበቃው የዋለልኝ መንፈስ ነው። ቅንጅትን ፈጥሮ የአፈረሰና መድረክን የተካ የዋለልኝዝም አስማትና ጥበብ ነው።" (መስመር የእኔ)

ፀሐፊው ዋለልኝዝም የሚሉትን መንፈስ ፈጥረው ከ1952 ጀምሮ ሀገራችን ላለፈችባቸው የለውጥ እንቅስቀሴዎች በመላ አድራጊ ፈጣሪ አድርገውታል። የወደፊቱ ተስፋችንም ወሳኝ አድርገው ሹመውታል። ተስፋ አስቆርጠው፣ ለወያኔው (ለመለስ ምክትል ተብዬ) ሃይለማርያም በእጅ መንሻነት

ሊያስረክቡን። ለዚህም ግባቸው መሳካት ባለፈው ለተሻለ የሥርዓት ለውጥ፣ ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲና ለአንድነት የተደረጉ ተጋድሎዎችን፣ የተከፈሉ መስዋዕትነቶችን እንዲንረሳ ይሻሉ። በየጊዜው የተነሱትንም ሆነ አሁን ያሉትን የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ጎለት (መቀፍቀፊያ ዕቃ) ሆነው የሚፈጥሯቸው ሰበቦች በየጊዜው የሚጫኑብን ብልሹ አገዛዞች መሆናቸውን እውነታ ሊያስቱን ይሞክራሉ። ሌላው ቀርቶ በባዕዳን ሃይ የሚባሉትም ሆኑ ጠባብ ጎሳዊ ወይም ቡድናዊ ጥቅም የሚያራምዱት፣ በተቃዋሚነት ህዝቡ ውስጥ መንቀሳቀስ እንዲችሉ የተመቻቸ እድል የሚፈጥሩላቸው እኒኚሁ ብልሹ አገዛዞች ናቸው።

በሌላው የታሪካችን አምድ ላይ ግን በተቃራኒው የሀገራችንን መንግሥታዊ አስተዳደር ለማሻሻል እና የሚዛመዱትንም ችግሮች ለመፍታት ብሄራዊ ራዕይ ሰንቀው የተነሱ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ነበሩ፣ አሁንም አሉ። በዚህም ራዕያቸው በዚያና በአሁኑ ጨለማ አገዛዝ ላይ የተስፋ ኩራዝ አብርተውልን አልፈዋል፣ ክቡር ዋጋም ከፍለውልናል።

የኢትዮሚዲያ ፀሐፊ ግን ሁሉንም፣ ጠባብ ብሄርተኛውንም፣ ሀገር አቀፍ ራዕይ ያነገበውንም፣ መብቴ ይከበር ብሎ በመቆሙ ግድያ፣ መከራ ችግር የተቀበለውንና በመቀበል ላይ ያለውን፣ ይህንኑ ጭቆና ያደረሱትን ወይም እያደረሱ ያሉትን የደርግንም ሆነ የወያኔ አገዛዞች አንድ ላይ በመጨፍለቅ ዋለልኚዝም ብለው በፈጠሩልን መነፀር እንዲናያቸው ይፈልጋሉ። ህዝባችን ለወረደበት እና እየወረደበት ላለው መዓት ምክንያቱ አፍነው ይዘውት የነበሩት አሁንም የያዘው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሳይሆን የትውልድ እርግማን ነው ብለው ይሰብኩናል።

በእውነት ላስተዋለ ግን ታሪክ የሚያሳዬን ሌላ ነው። በየጊዜው የሚነሱት አገዛዞች የሕዝብን ጥያቄ አፍነው በመያዛቸው፣ ህዝቡ መጭ እድሉን በራሱ ሥልጣንና እሳቤ እንዳይመራ እንቅፋት በመሆናቸው፣ ህዝቡ ወደፊት ቀድሞ

ዕድገትንና መሻሻልን ሲጠይቃቸው፣ እነሱ ወደ ሁዋላ ቀርተው፣ በአገዛዝ ልጓማቸው ሸብበው ይዘው፣ እንጋልብህ ሲሉት የተካሄደ እና እየተካሄደ ያለ ትንቅንቅ ነው ታሪካችን የሚያስነብበን። በዚህ የትንቅንቅ ታሪክም ዋለልኝ እና ጓደኞቹ የነበሩበትንና አሁንም በተለያየ መልኩ እየታዬ ያለውን የእኩልነትና የፍትህ እጦት በመንቀስ፣ የአረገዘውንም ችግር ዘመንና ትውልድ ተሻግረው በማመላከት ኮከብ ሆነው አልፈዋል።

እውነት ነው እኒሁ ፀሐፊም ሊክዱ እንዳልቻሉትና አሞግሶ ለመወንጀል ሊጠቀሙበት እንደሞከሩት ዋለልኝና ያ ትውልድ ማርክሲስትነት፣ ስርነቀልነት እና መስዋዕትነት ከመግለጫ ፀባያቱ ውስጥ ዋናዎቹ አላባዊያን (ኤለመንትስ) ነበሩ።

ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ልክ እንደኒሁ ፀሀፊ ሌሎችም ያን ትውልድ ለመኮነን ግራ ዘመምነቱን መጥቀሳቸው የተለመደ ሆኗል። ሁሉም የሚስቱት ሀቅ ግን በዘመኑ የግራው ርዕዮተ-ዓለም በዓለም ላይ የገነነ ተቀባይነት እንደነበረውና፣ የአፄው አገዛዝ የጡት አባትም አሜሪካ የነበረች መሆኗን ነው። ደግሞም እኮ የንጉሡ አገዛዝ የተዋቀረው ከእዚቹ ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ፤ ከሌሎቹም ሀገሮች ልምድ በተወሰዱ የአስተዳደር ፈሊጦች ሚስቶነት (ድብልቅ) መሆኑ ነው። አገዛዙም ተቃዋሚውም ኢትዮጵያዊነትም ፀባይ ነበራቸው፣ ከውጭም የወሰዷቸው ጉዳዮች ነበሩ። በተጨማሪም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በራሱ ትልቅ የማህበረሰብ ሳይንስና እጅግ ብዙ ለህብረተሰብ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጡ ታላላቅ ዕውቀቶችንና ጥበቦችን የያዘ መሆኑ ሊረሳ አይገባም። ጠዋት ማታ የሚኮንኑት ምዕራባዊያን ሀገሮች ሳይቀሩ ከዚሁ ርዕዮተ-ዓለም እየወሰዱ ያለባቸውን ችግር ለማስተንፈስ ግልጋሎት ላይ የሚያውሏቸው በርካታ ጉዳዮች ለምሳሌ መንግሥታዊ ጥቅማ ጥቅሞች መኖራቸውንም የኛዎቹ ከጳጳሱ ቄሱዎቹ ልብ ሊሉት ይገባል። እናም ያ ትውልድ የግራውን ርዕዮት መደገፉ ነው? ወይስ ያን ምርጫህን በነፃነት አትገልጽም ብለው የእመቃና የግድያ ዝናብ ያዘነቡበት አገዛዞች

ጥፋተኞቹ? ለመሆኑ በዘመናችን ገኖ ተቀባይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ መድብለ-ፓርቲ አስተዳደር ከግሪክ ፈላስፎች ተወልዶ ዓለም ላይ የተዘራ አይደለምን? ወይስ ሥርዎ ውልደቱ ፍፁም ኢትዮጵያዊ የሆነ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሃብትና ማህበራዊ ዕድገት ከወያኔ ወይም ከሌላ አንድ ሳንቲም ግልባጩ ከዓረና ትግራይ እስከሚፈጠረልን ዓይናችንን በሌላው ዓለም ላይ እንድንጨፍን ነው የሚታሰበው?

ሥርነቀልነትንና መስዋዕትነትን በተመለከተም ዋለልኝም፣ ማርታም፣ ጥላሁንም፣ ሌሎቹም ሌሎቹም የህይወት ዋጋ ከፍለው ያሳዩት ይህንኑ ነው። ተስፋዬ፣ ዳሮ፣ ኡስማን፣ ወዘተ ሺህዎችም ደርግን ተጋፍጠው የተሰውት ይህንኑ የዓላማ ፅናትና ቆራጥነት ወርሰው ነው። የነኝህ የነኝህ ዓይነቶቹን ብሄራዊ ራዕይ አንግበው እራሳቸውን አቃጥለው በጨለማው የሀገራችን ሰማይ ላይ ተወርዋሪ ኮከብ ሆነው የነበሩትን አደራ በመሸከምም ወያኔን በመታገል የተሰውት ጋይም፣ አሰፋ፣ ተስፋዬ፣ ሽብሬ፣ ወዘተዎችም፣ የሕዝብ ጥያቄዎች መልስ እስካላገኙ ድረስ የተገለፁት ባህርያት ከትውልድ ወደትውልድ ተወራራሽ መሆናቸው የግድ እንደሆነ አስረጂ ናቸው። ባህርያቱ ደግሞ ትላንትም ሆነ ዛሬ፣ ነገም ጭምር፣ አንድ ማህበረሰብ ህልውናውን ጠብቆ፣ በራሱ ቆሞ ለመኖር እና በዕድገት እሽቅድምድም ከሌሎቹ በልጦ ለመገኘት ምንጊዜም የሚያስፈልጉት እሴቶቹ ናቸው። ቁልፉ ጥያቄ በማህበረሰቡ ዘንድ የመሪነቱን መሪ የያዙት የሚመሩትን ማህበረሰብ የለውጥ ምት (ጥያቄ) ምን ያህል እያዳመጡ፣ በምን ያህል ፍጥነትና አሳታፊነት አስፈላጊውን የማስተካከያ ለውጥ ያካሂዳሉ ነው? አፄው እነታከለ ወልደሐዋርያትን፣ እነበላይ ዘለቀን፣ እነገርማሜና መንግሥቱ ንዋይንና የመሳሰሉትን ጠያቂዎችና ደፋሮች ሲያጠፉ፣ ግብርና ሚኒስቴር ያረቀቀውን የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ረቂቅ እንኳ ህግ አድርጎ ከመደንገግ ታቅበው፣ ከህዝቡ የለውጥ ፍላጎት ጋር መራመድ አቅቷቸው፣ ሲንቀረፈፉ ነው፣ እራሳቸውንም ህዝቡንም ለጭራቁ ወታደራዊ አገዛዝ አሳልፈው ያስረከቡት። ወታደራዊው አገዛዝም እንደዚያው። ታዲያ ከጊዜው የማህበረሰቡ ጥያቄዎች ጋር በመራመድ፣

እራሱን በመለወጥ ፈንታ እመቃንና ግድያን፣ በ"ስልጣን ወይም ሞት!" መፈክር ለሚያደነቁር፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ፈሊጥን ሙጥኝ ላለ አገዛዝ ምን የመለወጫ መንገድ አለው?

በምንስ ተጠየቅ ነው በሕብረ-ብሔርነት በመደራጀት፣ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር የተለያዩ አማራጮችን አቅርበው የሚታገሉት ለምሳሌ ኢሕአፓ፣ ግንቦት ሰባት እና ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው ለጎሳ ነፃነት የሚንቀሳቀሱት ለምሳሌ ኦነግ፣ ሻዕቢያ በአንድ የሚመደቡት? ፀሀፊው ሁሉንም በአንድ ከረጢት አስገብተዋቸዋል። ይህ ሁሉ ድካማቸው ደግሞ ዋለልኝና ያን ትውልድ አባት አድርገው፣ ዋለልኚዝም የሚል የወል መጠሪያ በመስጠት፣ ሁሉንም በአንድ ላይ ለመቦደን ነው። ሁሉም፣ ልክ እንደ ወያኔ ናቸው በሚል ሥሌት፣ ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ በሚል ተስፋ አስቆራጭ ስልት ለወያኔ የቋንቋ ከፋፍለህ ግዛው ፌዴራላዊ አገዛዝ ሰጥ ለጥ ብለን እንድንመቻች ስለፈለጉ። የወያኔው ቁንጮ መለስ ተናገረ የተባለውን፡

“ጠ/ሚኒስትሩ ለአሜሪካኖቹ ያሉት … አዎ እኛ የምናካሂደው ከናንተ የተለየ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ነው። … በዚህም ብትቃወሙን ይገባናል። … ተቃውሟችሁንም በጸጋ እንቀበዋለን ... ግን እኛን መቃወም የኛን ተቃዋሚዎች ደጋፊ ሊያደርጋችሁ አይችልም … ምክንያቱም ከኛ የተሻሉ አይሆኑም … እኛም እነሱም ለዲሞክራሲ አንበቃም ግን እኛ እንሻላችሁዋለን … "

የሚል አባባል በመጥቀስ ስለእውነተኛነቱ ያደንቁታል። የወያኔን የተለመደ የማደንቆሪያ ውሸት መልሰው ሊያሳምኑን ይሞክራሉ። እርግጥ ነው፣ መለስ እንዳለው ለአሜሪካኖቹ ባለው አገልጋይነት ከሌሎቹ ይልቅ እሱ የተሻለ ሊሆን ይችላል። የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ሳያቅማማ አሳልፎ የሚሰጥ ነውና። እንደትላንቶቹ አገዛዞች ሁሉ ዛሬም ግን ለህዝቡ የዴሞክራሲ እና የሥልጣን ባለቤትነት ጥያቄ መልስ አልሰጥ ያለው፣ መብታችን ይከበር፣

የዜግነት መብታችን እኩልነትና ሉዐላዊነት ይረጋገጥ ባሉ ሺህዎችን የገደለው፣ ያሰረው፣ በአድሎአዊ አገዛዙ ሚሊዮኖችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ቀፍድዶ የያዘው የህወሓት/ኢህአደግ አገዛዝ ነው። እነጋይም፣ አሰፋ፣ ተስፋዬ፣ ሽብሬ ወዘተ ግደሉን ብለው አልተገደሉም። እነጸጋዬ፣ አበራሽ፣ ስጦታው፣ አምሃ፣ ወዘተ ለዓመታት በጉርጓድ እስር ቤት እንታሰር ብለው በመምረጣቸው አይደለም ላለፉት 19 ዓመታት መዳረሻቸው የጠፋው። የ1997 ምርጫን ተከትሎ በአዲስ አበባ ብቻ በቀናት ውስጥ ከ200 በላይ ንፁሃን ቀንበጦች፣ በጠራራ ፀሐይ በአግዐዚ የተቀጠፉት ከመለስና ከተቀሩት ጠባቦች የበለጠ ብሄራዊ ራዕይ አልመው በመነሳታቸውና ለዴሞክራሲ መብታቸው መከበር በመቆማቸው ነው። መለስ እና ደጋፊዎቹ ሊሰብኩ እንደሚሹት፣ አለዚያም ምእራባዊያኑ ጌቶቹ አንድም በዘረኛ ድንቁርናቸውና ንቀታቸው፣ ሁለትም በተጨፈኑ እናሙኛችሁ ማጃጃያቸው ሊያሳምኑ እንደሚሞክሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቱን፣ የሀገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን ቁልፍ ለመቀበል ብቃት የሚያንሰው አይደለም። ይህን እውን ለማድረግ ትግል ከጀመረ ብዙ ዓመታት አልፈውታል። አሁንም ትግሉን አፋፍሟል።

ለዚህ ትግል ከግቡ መድረስ ደግሞ አሁንም የዚያ ትውልድ መለዮ ፀባይ ከነበሩት ውስጥ ሥርነቀል የሥርአት ለውጥ ፈላጊነት እና መሥዋዕትነት የግድ ናቸው። የርዕዮተ-ዓለም ምርጫውን ለየድርጅቶቹ ብንተወው። በተረፈ ግን ወያኔን በመለማመጥ ወይም ዳግማዊ ወያኔን (የመለስን ቡድን) በሳልሳዊ ወያኔ (በዓረና ትግራይ) በመለወጥ እውነተኛ ድል የሚመጣ አይሆንም። ወይም የአብርሃም በላይ አምደኛ እንደሚሉት ወያኔ ለእድሜ ማስቀጠያነት ባሻው ጊዜ እያስረገዘ፣ ባሻው ጊዜ በሚያስወልዳቸው ሽማግሌዎች አለዚያም የሃይማኖት አባት ተብዬዎች በሚያቀነባብሩት የገዳይ ከገዳይ እርቅ አይደለም። ብሄራዊ ዕርቅ በመላው ሀገሪቱ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች መከበርን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥን እውን ከሚያደረግ ሂደት ጋር ሲቀናጅ እንጂ።

የሥልጣን መሪውንና ወሳኝነቱን ወያኔ እንደተቆጣጣረው ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ሆኖ ሳለ፣ የግንባር ሥጋ ሆነው ለይምሰል እንዲረዱ ከየጎሳው የተለቀሙ ጥቂት አገልጋዮች እየተበወዙ በመቀየራቸው፣ ይህንን እንደ አንድ የለውጥ እምርታ ወስደን ትግላችንን እንዲናቀዘቅዝም እኒሁ የኢትዮሚዲያ ፀሐፊ ይመክሩናል። በደቡብ ኢትዮጵያ ለታጠበበት የንፁሃን ደም እና ለታማኝ አገልጋይነቱ በሽልማትነት ምክትል ጠቅላይ ሚ/ትር የሆነውን የሃይለማርያም ደሳለኝንም ተስፋ አድርገን እንዲንቆይም፡ “... እንደ ሃ/ማርያም አይነት አዲስ ሰዎች ወደ ፖሊቲካ መድረኩ መውጣት ትልቁ አስተዋጽዖ (እንደ ትምህክተኞቹ በዘር፣ እንደ ዋለልኞቹ በመስዋዕትነት) የስልጣን entitlement (ይገባናል) ደዌ ያልተጠናወታቸው በመሆኑ ስልጣን በድርጅት ውስጥ ከግለሰብ ወደግለሰብና በአገር ደረጃም ከድርጅት ወደ ድርጅት በሰላምና በርጋታ (smoothly) እንዲሸጋገር ስለሚረዱ ነው። ..” በማለት ይነግሩናል። ይኸ ምክራቸው አንድ አባባል አስታወሰኝ፣ "ግዛኝ ግዛኝ ብለው ሊሸጠኝ አማረው” የሚለውን። የመለስም ይሁኑ የስዬ ደጋፊዎች እንደማንም አምባገነን አምላኪዎች ሁሉ የራሳቸውን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ማመን ጀምረዋል ልበል? ወይስ በማን ዘር የበላይነት ሀገሪቱ እየተመራች እንደሆነ ለመረዳት 19 ዓመት ያንሰናል ብለው አስበው ይሆን?! ለመሆኑ ሃይለማርያምስ የዘር ድርጅት አመራር ተብሎ አይደለም እንዴ በወያኔ አገልጋይነት እየሠራ ያለው?

እንደነሃይለማርያም ደሳለኝ ዓይነቶቹን በደቡብ ኢትዮጵያ — በወላይታና በአዋሳ - በጨፈጨፏቸው ንፁሃን ዜጎች ደም የታጠቡ የወያኔ አገልጋይ ወንጀለኞች የተስፋችን ሙሴዎች ናቸው ብለው ሊሰብኩን የሚጥሩት እኒሁ ፀሐፊ የዚያ ትውልድ አባላት ላይ በሀገራቸው ፖለቲካ ሙሉ ተሳትፎ ከማድረግ እንዲታቀቡም ይጠይቃሉ። ከነመንግሥቱ ንዋይ የ 1952 መፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ወዲህ ጀምሮ እስካሁን ያለውን መላውን ኢትዮጵያዊ ዜጋና ድርጅት ሁላ በወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሰበብ ተዘፍቀን

ላለንበት ችግር ተጠያቂ በማድረግ፣ በሀገሩ ፖለቲካ መሳተፍ የለበትም የሚል ማዕቀብ እንዲነጥል ጥሪ ያደርጋሉ። ስለዴሞክራሲ እያወሩ ፀረ-ዴሞክራሲ እንሁን ይሉናል። ኢትዮጵያ ከመላው ሕዝቧ ውስጥ ከፍተኛ ዕድሜ ካስመዘገበው አባት ወይም እናት አንስቶ እስከ አሁኗና እስከመጭዋ ሚሊሰከንድ የሚወለዱት ህፃናቷ ሀገር ነች። እኩልነት ሰፈነባት የሚባለውም ሁላቸውም ዜጎች የባለቤትነታቸውና የተሳትፏቸው መብት ሲረጋገጥ ነው። ያች ኢትዮጵያም ከእያንዳንዳቸው እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው አስተዋጽዖዋቸውን ትሻለች። ያች ኢትዮጵያም እውን ልትሆን የምትችለው ደግሞ ትላንትም ዛሬም ወገቤን ሳይሉ ብሔራዊና ህዝባበዊ ራዕይ አንግበው፣ ፅናትን ታጥቀው፣ መስዋዕትነትን ለመቀበል ሳያፈገፍጉ ትግላቸውን የቀጠሉትን ጀግኖች ስንከተል፣ ገድላቸውን ስናከብር፣ ዓርማቸውን ተረክበን፣ ትግላቸውን ስንቀጥለው ነው። ገዳዮቻቸው የጀግኖቻችንን አካል እንደገደሉት እኛም የሕዝባዊ ኮከቦቻችንን ታሪክ ገድለን፣ ለጠላቶቻቸው እጅ ሰጥተን አይደለም። አሁንም ሀገር አድን የህልውናና የዴሞክራሲ ትግላችን ለድል እንዲበቃ በስር-ነቀል ለውጥ ወያኔን ማስወገድ የግድ ይላል፣ እንደትላንቱ ሁሉ ዛሬም መስዋዕትነትን ይጠይቃል። የዋለልኝም ዋና መልእክት ይህ ነው።

ክብር ለሠማዕታቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ahmedyimam@hotmail.